# የሲያትል ማዳኛ እቅድ (Seattle Rescue Plan)

**የሲያትል የኮቪድ-19 የማገገሚያ የገንዘብ ድጋፍ አዲስ መረጃ፣ ሓምሌ 2023**

የሲያትል ማዳኛ እቅድ (Seattle Rescue Plan) ከተማዋ የፌደራል የእርዳታ ገንዘብን እንዴት ባለ መልኩ ከተማችን ከ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ የጤና እና የቁጠባ ተጽእኖዎች እንድታገግም በማድረግ ስራ ላይ እያዋለችው እንደሆነ የሚያሳይ ዕቅድ ነው። ሲያትል የገንዘብ ድጋፉ ጥቅም ላይ ሊውልባቸው የሚችልባቸው ቅድሚያ የሚሰጣቸው አምስት ቦታዎችን ለመለየት ህዝባዊ ውይይቶችን እና የአስተያየት መሰብሰቢያ ዝግጅቶችን አካሂዳለች፥

- መኖሪያ ቤት እና የቤት እጦት ($100.5 ሚሊዮን)
- ደህንነት/ጤንነት እና አገልግሎቶችን መልሶ ማስጀመር ($67 ሚልዮን)
- የነዋሪዎች እና የአነስተኛ የንግድ ተቋማት ማገገሚያ ($51 ሚልዮን)
- ደህንነት እና የአእምሮ ጤና ($5.4 ሚልዮን)
- የከተማዋን ሰራተኞች እና አገልግሎቶችን መደገፍ ($78.1 ሚልዮን)

### የሲያትል ማዳኛ እቅድ (Seattle Rescue Plan) የገንዘብ ድጋፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቦታዎች

**ጠቅላላ: $301.9 ሚሊዮን**




## የ2022-2023 ዋና ዋና ፍጻሜዎች

- ከ 350 በላይ ከሆኑ የማህበረሰብ ድርጅቶች እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ጋር በትብብር ስራዎች ተሰርቷል
- ከ 3,700 በላይ ለሆኑ አነስተኛ ንግዶች አገልግሎቶችን ሰጥተዋል እና ከ 50 ለሚበልጡ የንግድ ማህበራት እርዳታን አቅርቧል
- ከ 4,600 በላይ ለሚሆኑ አርቲስቶች እና የባህል ሰራተኞች ድጋፍን ሰጥቷል
- ከ700,000 በላይ ተሳታፊዎችን የሳቡ የህዝብ ዝግጅቶች ደግፏል
- 411 አዳዲስ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤቶችን የያዙ አራት ሕንፃዎችን ገዝቷል
- ከ 1,000,000 በላይ የሆኑ ወደ ምግብ ባንክ የሚደረጉ ጉብኝቶችን በመደገፍ እና ለ300,000 በላይ ምግቦች የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል
- ለ 690 ሕጻናት ነፃ የሕጻናት እንክብካቤ አገልግሎትን በማቅረብ እና በተጨማሪም ለ311 ሕጻናት፣ የሕፃናት እንክብካቤ አገልግሎቶችን ለሚሰጡ ፕሮጀክቶች የገንዘብ ድጋፍ ሰጥቷል

## መኖሪያ ቤት እና የቤት እጦት ($100.5 ሚሊዮን)

**ዓላማ፡** ነዋሪዎች አስተማማኝ፣ ተመጣጣኝ፣ እና የተረጋጋ የመኖሪያ ቤት አማራጮች እንዲሁም ጊዜያዊ የመጠለያ እና የአገልግሎቶች ግብዓቶችን የማግኘት ዕድል አላቸው።

**ምሳሌዎች፡** የቤት እጦት ላጋጠማቸው ሰዎች፣ የአጭር ጊዜ የኪራይ ድጋፍ፣ አስቸኳይ የኪራይ እርዳታ፣ ከቤት እጦት ወጥተው ፈጣን በሆነ መንገድ ቤት መልሰው እንዲያገኙ ለማድረግ መጠለያ እና ጥየቃን በማድረግ በተመጣጣኝ ዋጋ ጥቅም ላይ የሚውሉ 4 ሕንፃዎችን ገዝቷል

## ደህንነት/ጤንነት እና አገልግሎቶችን መልሶ ማስጀመር ($67 ሚልዮን)

**ዓላማ፡** ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው እና ሃብት የሌላቸው ቤተሰቦች እንደ ምግብ እና የመኖሪያ ቤት ያሉ መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ሊያሟሉ ይችላሉ፣ እንደዚሁም ለመዝናናት እና ለተሻለ ጤንነት፣ ደህንነታቸው የተጠበቁ የውጪ እና የህዝብ ቦታዎችን ይጠቀማሉ።

**ምሳሌዎች፡** አዲስ ሰራተኞችን ለመቅጠር እና ነባሮቹን በስራ ላይ ለማቆየት እንዲረዳ ለህፃናት እንክብካቤ ሰራተኞች ተጨማሪ ክፍያ ማድረግ፣ ለልጆች እንክብካቤ ተቋማት እና ለተማሪዎች የትምህርት ክፍያ እገዛን ማድረግ፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነዋሪዎች ቀጥተኛ የገንዘብ ድጋፍ፣ የማህበረሰብ ምግቦች፣ የቤተ-መጽሐፍት ሰዓቶችን ወደ ነበሩበት መመለስ

## የነዋሪዎች እና የአነስተኛ የንግድ ተቋማት ማገገሚያ ($51 ሚልዮን)

**ዓላማ፡**ሰዎች እና አነስተኛ ንግዶች ከኮቪድ-19 ተጽዕኖዎች በኢኮኖሚ ለማገገም እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።

**ምሳሌዎች፡** የስራ ስልጠና እና የቅጥር አገልግሎቶች የሙሉ ሰዓት ስራ ለማይሰሩ ሰራተኞች እና ከሚገባቸው በታች ለተቀጠሩ ሰራተኞች፣ ለአነስተኛ ንግዶች ቀጥተኛ የገንዘብ ድጋፍ፣ የኪነጥበብ እና የባህል ድርጅቶችን በአስተማማኝ ሁኔታ እንደገና ለመክፈት እና ሰራተኞችን ለመቅጠር የሚያስችላቸው ድጋፎችን ማድረግ፣ ከቤት ውጭ ለመመገብ እና ለሽያጭ ሲባል የመተላለፍ መብት ፈቃድ መስጠት፣ ቆሻሻ እና የግድግዳ ስዕሎችን ማስወገድ

## ደህንነት እና የአእምሮ ጤና ($5.4 ሚልዮን)

**ዓላማ፡** በኮቪድ-19 ያልተመጣጠነ ተጽእኖ የደረሰባቸው ሰዎች የባህሪ እና የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችን፣ እና የጥቃት መከላከል እና የጣልቃ መግባት ድጋፎችን ማግኘት ይችላሉ።

**ምሳሌዎች:** በስርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶችን ምላሽ የሚሰጡ አገልግሎቶች; ለወጣቶች እና ለቤተሰቦቻቸው የባህሪ እና የአእምሮ ጤና ኢንቨስትመንቶች፣ ተንቀሳቃሽ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችን ማስፋፋት

## የከተማዋን ሰራተኞች እና አገልግሎቶችን መደገፍ ($78.1 ሚልዮን)

**ዓላማ፡** የሲያትል ከተማ በአዲሱ የድህረ-ወረርሽኝ አካባቢ በአካል አገልግሎቶችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስቀጠል ዝግጅት ያላት እና ከወረርሽኝ ማገገሚያ የገንዘብ ድጋፎችን እና ጥረቶችን በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተዳደር የሚያስችሉ አቅሞች አሏት።

**ምሳሌዎች:** የሲያትል የእሳት አደጋ መከላከያ ክፍል የመጀመሪያ ምላሽ ሰጪ የደመወዝ ወጪዎች፣ የከተማዋ ሰራተኛ የኮቪድ ክትባት ማረጋገጫ ስርዓት፣ ወደ ቢሮ እና ወደ ርቀት ስራ መመለስን ለመደገፍ የፋሲሊቲ እና የቴክኖሎጂ ኢንቨስትመንቶች